# LAKE CITY COMMUNITY CENTER

# መልሶ ግንባታ

## የፕሮጀክት ግብ

Lake City Community Center የLake City ሰፈር ታሪክ ወሳኝ አካል ሲሆን፣ ለማህበረሰብ እንቅስቃሴዎች ማዕከል ሆኖ ሁሉንም ዕድሜ እና ባህል ያላቸውን ሰዎች በማሰባሰብ አገልግሏል። በ2023፣ እሳት የሕንፃውን አብዛኛውን ክፍል አወደመው፣ እና የማህበረሰብ ማዕከሉም ፈረሰ።

በ2024፣ ሲያትል መናፈሻ እና መዝናኛ (Seattle Parks and Recreation) ከDepartment of Neighborhoods ጋር በመተባበር የማህበረሰቡን ለአዲሱ ማዕከል ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች በተሻለ ለመረዳት የሕንፃ ፍላጎት ግምገማ አካሂደዋል። በ2025፣ ከተማው Mercy Housingን መልሶ ግንባታውን እንዲመራ መረጠ፣ ይህም በላይኛው ፎቅ ላይ ከ94 በላይ ተመጣጣኝ የኪራይ ቤቶችን እና በመሬት ደረጃ አዲስ የማህበረሰብ ማዕከልን ያካትታል። ይህ ፈጠራ ያለው ንድፍ ተመጣጣኝ ቤቶችን፣ አስፈላጊ አገልግሎቶችን እና የጋራ ማህበረሰብ ቦታዎችን በማጣመር ነዋሪዎች የሚኖሩበት፣ የሚሰበሰቡበት እና የሚያድጉበት ምቹ ቦታ ለመፍጠር ለCity of Seattle የመጀመሪያው ይሆናል። ሲያትል መናፈሻ እና መዝናኛ (Seattle Parks and Recreation) ከOffice of Housing እና ከDepartment of Neighborhoods ጋር በመሆን አዲሱ የማህበረሰብ ማዕከል የLake City ማህበረሰብን የአሁኑንም ሆነ የወደፊቱን ፍላጎት ማሟላቱን ለማረጋገጥ በሕዝባዊ ስብሰባዎች የማህበረሰብ አስተያየቶችን መሰብሰብ ይቀጥላሉ።

ግንባታው በ2026 ክረምት ይጀምራል ተብሎ ይጠበቃል።

## የፕሮጀክት መርሐግብር

እቅድ ማውጣት እና ዲዛይን:- 2024-2026 ግንባታ: 2027-2028 ማጠናቀቂያ: 2028

## ለፕሮጀክቱ መረጃ


@ Asmita.Poudel@seattle.gov 206-549-0827

seattle.gov/parks/about-us/projects/lake-city-community-center-redevelopment


繁體中文 Español Tiếng Việt Soomaali አማርኛ 한국어 Tagalog

Seattle Parks & Recreation

